MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

# የወደፊታችንን አብሮ መገንባት

## ተማሪዎች፣ መምህራን፣ እና ማህበረሰብ

### ራእይ

ለአያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀውን ሕዝባዊ ትምህርት በማቅረብ ትምህርት እንዲሰርፅ እናደርጋለን።

### ተልእኮ

እያንዳንዱ ተማሪ በኮሌጅም ሆነ በስራ ስኬታማ እንዲሆን አካዴሚያዊ፣ የችግር አፈታት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ችሎታዎች ይኖሩታል።

### የአላማ ፍሬ ነገር

ሁሉም ተማሪዎች በወደፊት ኑሮአቸው እንዲለሙ/እንዲበለፅጉ ማዘጋጀት

### አይነተኛ ተፈላጊዎች

- ትምህርት
- ግንኙነቶች/ዝምድናዎች
- ክብር
- ብልጫ
- ፍትህ



MCPS
Rockville, Maryland

WWW.MONTGOMERYSCHOOLSMD.ORG

## BOARD OF EDUCATION

Mr. Christopher S. Barclay
*President*

Mr. Philip Kauffman
*Vice President*

Ms. Shirley Brandman

Dr. Judith R. Docca

Mr. Michael A. Durso

Mrs. Patricia B. O'Neill

Mrs. Rebecca Smondrowski

Mr. Justin C. Kim
*Student Member*

**የትም/ቤት አስተዳደር**

Dr. Joshua P. Starr
*Superintendent of Schools*

Mr. Larry A. Bowers
*Chief Operating Officer*

Dr. Beth Schiavino-Narvaez
*Deputy Superintendent of School Support and Improvement*

Dr. Kimberly A. Statham
*Deputy Superintendent of Teaching, Learning, and Programs*

## የወደፊታችንን አብሮ መገንባት

### ተማሪዎች፣ መምህራን፣ እና ህብረተሰብ

**የስልታዊ ፕላን መዋቅር** ከMontgomery County Public Schools (MCPS) የሚመረቁ ተማሪዎች ለኮሌጅ ወይም/እና ወደ ስራ አለም ለመቀላቀል ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ያለንን ቁራጥነት አጉልቶ ያሳያል። ተማሪዎቻችን ባሳዩት ልዩ ውጤታማነት፣ የላቁ ሰራተኞቻችን፣ እና በድርጅታዊ ቅልጥፍና ምክንያት MCPS በሃገሪቱ እጅግ ስኬታማ ከሆኑት የትም/ቤት ዲስትሪክቶች እንዱ መሆኑ የታወቀለት ነው። ቢሆንም፣ ሁሉም ተማሪዎች በእጅግ ከፍተኛ ደረጃ ውጤ እስኪያስገኙና በአለም አቀፍ ደረጃ ለመወዳደር ዝግጁ እስኪሆኑ ድረስ ተግባራችን ተሟልቷል ማለት አይቻልም። አካዴሚያዊ ስኬት በዘር፣ በትውልድ፣ ወይም በማህበራዊ/ኤኮኖሚያዊ ደርጃ መተንበይ እስከማይቻልበት ደርጃ እስከሚደረስ እያንዳንዱንና ማንኛውንም ተማሪ ለማስተማር MCPS ግዴታ ገብቷል። የግኝት ልዩነት በሁሉም ወገኖች ጨርሶ እስኪጠፋ ድረስ ጥረታችን ይቀጥላል።

ለነገው ውስብስብ አለምና የስራ ቦታ የሚያዘጋጃቸው ስነ ጥበባትና ቴክኖሎጂን የመሳሰሉ ሌሎች መስኮችን የሚጨምር በአይነተኛ አርእስቶች ጥልቀት የለው አካዴሚያዊ እውቀት አግኝተው ተማሪዎቻችን ይመረቃሉ። ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ ወላጆችን፣ እና ማህበረሰቡን የሚያካትቱ በርካታ ባለቤቶችን በማስተባበር የተፈጠረው "የወደፊታችንን አብሮ መገንባት" የሚያተኩርባቸው ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያስፈልጓቸው — አካዴሚያዊ ብልጫ፣ የችገር እፈታት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ትምህርት ናቸው። ይህ መዋቅር ለተማሪዎቻችን፣ ለመምህራን፣ እና ለማህበረሰቡ ግቦቻችንን ለመምታት ጥራት ያለው መንገድ በመዘርጋት በነዚህ ሶስት ርእሶች የሚጠበቁትን ይዘረዝራል። MCPS ወደነዚህ ሶስት የችሎታ መስኮች የሚያመሩና እያንዳንዱ ተማሪ ከ2ኛ ደረጃ ባሻገር ለስኬት በሚገባ መዘጋጀቱን የማረጋገጥ የቦርዱን አይነተኛ ግቦች ለማንፀባረቅ መገልገያዎችን ማደራጀትና ማበልፀግ ይቀጥላል።

የMCPS ህብረተሰብ ለትብብር፣ ለፈጠራ፣ እና ለፍትህ ባህል ቆርጦ የተነሳ ነው ይህ ትኩረት ነው MCPSን ከሃገሪቱ ግንባር ቀደም የትም/ቤት ዲስትሪክቶች እንዱ ያደርገውና በሚመጡት ትውልዶች ተማሪዎቻችንን በእጅግ ከፍተኛ ደረጃ ማገልገል እንድንቀፅል የሚያስችለን። **ወደፊታችንን እብረን እየገነባን ነው።**

## የስኬቶቻችን አለካክ

**አምስት ዲስትሪክት አቀፍ ምእራፎች** የተማሪን ግስጋሴ ለመለካት ተመስርተዋል። የተማሪ ግኝት ለማሻሻል የስራ ፕሮግራሞች በማደራጀት ረገድ ትም/ቤቶችንና የስራ ክፍሎችን ለመምራት ለነዚህ ምእራፎችና የተያያዙ መረጃ አመልካቾች የአፈፃጸም ግቦች በመደራጀት ላይ ይገኛሉ።

### 3ኛ ክፍል

- ንባብ በብቃትና በላቁ ደርጃዎች

### 5ኛ ክፍል

- ንባብና ሂሳብ በብቃትና በላቁ ደርጃዎች
- ተስፋ፣ ተሳትፎ፣ እና ጤና/ደህንነት

### 8ኛ ክፍል

- ንባብና ሂሳብ በብቃትና በላቁ ደርጃዎች
- አልጀብራ 1 ከC ደረጃ ጋር ወይም ከዚያ በላይ
- ተስፋ፣ ተሳትፎ፣ እና ጤና/ደህንነት

### 9ኛ ክፍል

- እንግሊዝኛ ከC ደረጃ ጋር ወይም ከዚያ በላይ
- ሂሳብ ከC ደረጃ ጋር ወይም ከዚያ በላይ
- ብቃት

### ምረቃ—ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁ

- አልጄብራ 2 ከC ደረጃ ጋር ወይም ከዚያ በላይ
- AP 3 ወይም የተሻለ/IB 4 ወይም ከዚያ በላይ
- SAT 1650 ወይም የተሻለ/ACT 24 ወይም ከዚያ በላይ
- ተስፋ፣ ተሳትፎ፣ እና ጤና/ደህንነት
- በወቅቱ መመረቅ

### የአደረጃጀት ውጤታማነት መስፈርቶች

- የሙያ እድገት ስርአት
- የፅ/ቤትና የመምርያ ክፍል ስልታዊ እቅዶች
- የፅ/ቤትና የመምርያ ክፍል ውጤታማነት መስፈርቶች
- የሰራተኛ ተሳትፎ መጠይቅ

በሚመጡት ሶስት አመቶች፣ MCPS በተተለሙ አጠቃላይ የአፈፃፀም እድገትና በወገኖች መካከል የክንውን ክፍተት መቀነሱንና ያረጋገጣል የግኝት ልዩነቶችን ለማስወገድና የሁሉን ክንውን ለማሳደግ የስርእቱን ጥረት ለመከታተልና አቅጣጫ ለመስጠት መረጃዎቹ በተማሪ የዘር ጀርባና የአገልግሎት ወገኖች ይለያሉ።

## አካዴሚያዊ ብልጫ

### የMCPS ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው—

- ለድህረ-2ኛ ደረጃ ትምህርት እና/ወይም ለስራ ዝግጁ በመሆን ከ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት እንደተመረቁ ሁሉም ተማሪዎች ለስኬት ዝግጁ መሆናቸውን ማሳየት
- ውስብስብ ፅሁፎችን በማንበብ፣ ስለተለያዩ ጉዳዮች በመፃፍ፣ በተለያዩ ሁናቴዎች ንግግር በማድረግ፣ እና በቋንቋ በሚገባ በመጠቀም በተለያዩ የፅሁፍና የቃል ይዞታዎች ችሎታዎችን ማሳየት
- በፈታኝና በተለያዩ መስኮች ይዞታ መጋፈጥ
- የተማሩትን በአዳዲስ ሁኔታዎች ተግባራዊ ማድረግ

### የMCPS መምህራን የሚፈፅሟቸው—

- ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠበቅባቸው ማሳየት
- ከባህል አንፃር ተገቢና ምላሽ ሰጭ የሆነ ትምህርት ማቅረብ
- የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት የሚያረካ ትምህርት መለየት
- በበርካታና በተለያዩ እርምጃዎች ተማሪዎች የሚያውቁትንና መስራት የሚችሉትን መገምገም

## ችግርን በፈጠራ ማፍታት

### የMCPS ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው—

- ውስብስብና ያልተለመዱ ችግሮችን በሂሳዊና ፈጠራዊ አስተሳሰብ መፍታት
- ሃሳቦችን፣ ውጥኖችን፣ እና መረጃዎችን በቃል፣ በፅሁፍ እና በሌላ መገናኛ ዘዴዎች በጠራ ሁኔታ ማስቀመጥ
- ችግሮችን መተንተንና ማስረጃ አክሎ መደምደም/ማጠቃለል
- ትምህርትን ለማራመድ በተለያዩ የትምህርት መገልገያዎችና ቴክኖሎጂ መጠቀም

### የMCPS መምህራን የሚፈፅሟቸው—

- ተማሪዎችን አግባብና ፈታኝ ይዞታ ባለው ትምህርት መጥመድ
- በተለያዩ መንገዶችና የትምህርት ይዞታዎች ተማሪዎችን የሚያሰማራ አካባቢ መፍጠር
- ትምህርትን በባለቤትነት እንዲይዙ ተማሪዎችን ማስቻል
- ተማሪዎች አዳዲስና የፈጠራ መፍትሄዎች እንዲያፈልቁ ለማበረታታት ክፍትና ተጨባጭ ችግሮችን ማበርከት

## ማህበራዊ የስሜት ትምህርት

### የMCPS ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው—

- ብዙህንነትን /diversity/ እና ልዩነቶችን ዋጋ መስጠትና ማክበር
- ተስፋን፣ የግል ደህንነትን፣ እና ማህበራዊ ስነ ምግባርን የሚያራምዱ ገንቢና ጤናማ ውሳኔዎች ማከናወን
- ቻይነታቸውን፣ ትጉህነታቸውን፣ ማንነታቸውን ማወቅ፣ እና ለእድገት ያላቸውን አቋም መገንባት
- ትብብር፣ እርስበርስ መፅናናት፣ እና ግንኙነት የመገንባት ችሎታዎችን የሚያካትት የማህበራዊ ህልውናቸውን ማዳበር

### የMCPS መምህራን የሚፈፅሟቸው—

- ለብዙህነት፣ ለድፍረት፣ ለትብብር፣ ለገንቢ ክርክር፣ ለውጤታማ ግጭት አስታራቂነት ክብር መስጠት
- ጤንነትንና ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና አካላዊ ደህንነትን ማራመድ
- ተማሪዎችና መምህራን እርስበርሳቸው አወንታዊ ግንኙነት የሚያከናውኑባቸው እድሎች/አጋጣሚዎች መፍጠር
- ቻይነት፣ ትጋት፣ በራስ መተማመን፣ እና የእድገት ተቋምን ማስተማር አርአያም ማቅረብ
- በእርስበርስና በተማሪዎች ጠንካራ ጎኖች መገንባት

የማህበረሰብ አባላትና MCPS በተግባር በመሻረክ ሁሉም ተማሪዎች ለወደፊት ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ ትም/ቤቶችን በመደገፍ፣ ለመገልገያዎች መገኘት በዋስትና በመሳተፍ፣ ለተሞክሮ ትምህርት እድሎች በመፍጠር፣ እና የስልታዊ ፕላን መዋቅር ዋና ፍሬ ነገር በመደገፍ ዋስትና መስጠት።

## መሰረቱ፡- ድርጅት ፍሬያማነት

### MCPS የሚፈፅማቸው፡—

- ክብሮቻችንን የሚያንፀባርቅ ራሱን የሚያድስ ተማሪ ማህበረሰብ ለመገንባት፣ ከሁሉም ሸርኮቻችን ጋር በመተባበርና መከባበር ግንኙነት ማከናወን
- ለሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ስኬት መሰረታዊ የሆኑ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የንግድ ስራ እንቅስቃሴዎችና ደጋፊ አገልግሎቶችን ማቅረብ
- ውጤታማ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ዘላቂ ልምዶችን በማካተት፣ መገልገያዎችን ማደራጀትና ማበልፀግ
- ማስተማርንና መማርን የሚደግፉ የአሰራር ቅልጥፍና፣ የደንበኛ አገልግሎት፣ እና የጋርዮሽ ተጠያቂነት ስልታዊ ሂደቶች መመስረት
- ለብልጫ መቅጠርና የሁሉን መምህራን ችሎታ መገንባት
- ውጤታማ የሁለት አቅጣጫ ግንኙነት ማበረታታት

ሁሉም ተማሪዎች ለወደፊት እንዲበለፅጉ ማዘጋጀት፡ ለኮሌጅና ለስራ

**ስልታዊ የፕላን መዋቅራችን** የሚያተኩረው በሶስት እጅግ ከፍተኛ መስኮች ነው፡- አካዴሚያዊ ብልጫ፣ ፈጠራ ያለው የችግር አፈታት፣ እና ማህበራዊ ስሜታዊ ትምህርት። ማእከላዊው የአገልግሎቶች ቡድን የያንዳንዱን ትም/ቤት መረጃዎችና የመገልገያዎች ስርጭት በመተንተን ስራውን ከትም/ቤቶች ፍላጎቶች ጋር ያስማራል። በተጨማሪ፣ በሙያ መዳበር፣ በማህበረሰብ ተሳትፎ፣ እና በስልታዊ ጣልቃ ገብነት በመመስረት፣ እያንዳንዱ ትም/ቤትና ፅ/ቤት በትም/ቤት መሻሻል በማተኮር በሙያዊ የትምህርት እንቅስቃሴዎች ይሳተፋል።

የሁሉንም ትም/ቤቶች ጠንካራ ጎንና ፍላጎቶች ተገንዝቦና አውቆ ሁሉንም ለማገልገል እንድንችል የምንጠቀምበት አይነተኛ መሳርያ የትም/ቤት ድጋፍና መሻሻል መዋቅር ነው። የተመሰረተውም በርካታ የመረጃ ምንጮች በመጠቀም የተማሪን ስኬት በሚያራምዱ በአራት መስኮች ነው። በዚህ መዋቅር የተጠቀምንባቸው ናሙናዎች ከዚህ በታች ሰፍረዋል።

## የትም/ቤት ድጋፍና መሻሻል መዋቅር

### የተማሪ ውጤት መረጃዎች

**ዲስትሪክት አቀፍ ኢላማዎችና ምእራፎች**

- የስቴት ግምገማዎች
- ብቃት
- የምሩቃን ብዛት መጠን
- አልጀብራ 1 እና አልጀብራ 2 ውጤት C ወይም የተሻለ
- SAT, AP, IB

### የሚታዩ መረጃዎች

**የባለጉዳይ አስተያየት**

- የGallup ተማሪ፣ የመምህራን ተሰትፎ ዳሰሳ
- በMCPS የወላጅ ተሳትፎ ዳሰሳ

### የመተግበርያ መረጃዎች

**የትም/ቤት ማሻሻያ ፕላን**

ስርአተትምህርት 2.0

- የመተግበርያ መምርያ

የሙያ መማርያ ህብረተሰቦች (PLCs-Professional Learning Communities)

- የPLC ትግባሬ ዳሰሳ

### የአመራር መረጃዎች

- የሙያ እድገት ስርአት የአመራር ልምድ መለኪያዎች
- ባለከፍተኛ ውጤት ትምህርታዊ አመራር ልምዶች የሚያካትቱት፡-
  - አመራር — ለትም/ቤት መሻሻል - የትምህርት አሰጣጥ ትኩረትን ማብራራት
  - አመራር — ለፍትህ - ከፍተኛ የውጤት ደረጃ ላማግኘት እኩል አቅርቦትና እድል ለሁሉም ተማሪዎች መስጠት
  - አመራር — ለትምህርት የሙያ መዳበርን ማቀነባበርና PLCዎችን ከትምህርታዊ ትኩረት ጋር ማሰፋፋት
  - አመራር — ለከፍተኛ ተንቀሳቃሽ ቡድኖች - የትምህርታዊ አመራር ቡድን አባላት የትምህርታዊ አመራር ችሎታቸውን መገንባት

# ዝግጁነትና ስኬት

## እይነተኛ ግቦቻችን

### ትምህርት

**የምናምነው** እያንዳንዱን ተማሪ ማሳተፍ እንዳለብን፤ ትምህርት የሚገኘው የማወቅ ፍላጎትን በመኮቶኮትና ብርታትን፡ ትኩረትን እና ትጉህ ሰራተኛነትን በማበረታታት ነው፤ እናም የአዋቂ ትምህርትና ተሳትፎ ለተማሪ ትምህርት ቁልፍ ናቸው።

**ስለዚህ**፣ ሂሳዊ አስተሳሰብ፣ ችግር መፍታት፣ ተግባራዊ መጠይቅ፣ እና ድፍረት በተከታታይ እንዲሻሻሉ እናበረታታለን፤ ተማሪዎችን በተገቢና በጠንካራ አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ የትምህርት ተሞክሮዎች በማሳተፍ ፈልጎ ማወቅን ማራመድ፤ እና ልምዶቻችንን ለማሻሻል መግለጫዎችን ለመተንተንና ለማጥናት ራሳችንን መፈታተን።

### ግንኙነቶች

**እምነታችን፣** ለስኬታችን ትርጉም ያለው ትብብር ወሳኝ መሆኑ፤ ጠንካራ ሽርክናዎች የሚገነቡት በእምነትና በቀና ግንኙነት መሆኑ፤ እና ከተዥጎረጎረው ህብረተሰባችን ጋር ግንኙነት ለመገንባት የሌሎችን አመልካከቶችና ተሞክሮዎች መገንዘብ እንደሚፈለግብን፣ ነው።

**ስለዚህ**፣ የተማሪና የመምህራን አባላትን ይበልጥ ለማገልገል በግለሰብ ደረጃ እናውቃቸዋለን፣ በጋራ በተስማማንባቸው ግቦች ለመድረስ ከሽርኮቻችን ጋር በጥቅም በተመሰረተ ውሳኔ እሰጣጥ እንሳተፋለን፤ እና ትምህርትን ድጋፍ ለመስጠት ከተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ መማህራን፣ እና ከማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ግንኙነቶች እንገነባለን።

### ክብር

**እምነታችን**የያንዳንዱ ግለሰብ አስተዋፅኦ ለሕብረተሰቡ ትምህርት ዋጋ እንዳለው፤ ፍትሃዊ አያያዝ፣ ቀናነት፣ ግልፅነት፣ እና ታማኝነት በጣም ተፈላጊ መሆናቸው፤ እና የባህላችን፣ ጥቅሞቻችን፣ ችሎታዎቻችን፣ እና የጀርባችን መዥጎርጎር (diversity) የሚያጠናክረን ሃብት መሆኑ ነው።

**ስለዚህ**፣ መልካም ስነምግባር በየአቅጣጫው እናስከብራለን ግልፅ ንግግርም እናበረታታለን፤ እርስበርሳችን በፍትህና በቀናነት እንከባበራለን፤ የሌሎችን አስተያየቶች በግልፅ እናዳምጣለን፤ የአስተያየት ልዩነቶች ሊኖሩ መቻላቸውን እንቀበላለን።

### ብልጫ

**እምነታችን** ሁሉም ተማሪዎች ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁ ሆነው መመረቃቸውን ለማረጋገጥ የላቁ ደረጃዎች ለማስቀመጥ መመዘኛ መስመሩን ከፍ በማድረግ አስፈላጊ መሆኑን፤ በየእለቱ፣ ከማንኛውም የላቀውን እንድናገኝ የላቀውን መጠበቅ እንዳለብን፤ እናም የአእምሮ ንቃት መፍጠርና የግል እድገትን መደገፍ ሁላችንንም ለበለጠ እንድንሰራ እንደሚገፋፋ ነው።

**ስለዚህ**፣ ለማያቋርጥ መሻሻል ያለእረፍት እንገፋለን፤ ልምዳችንና ስራችንን በእጅግ ከፍተኛ ደረጃ እንይዛለን፤ እዳዲስ ሃሳብ አፍላቂነትና ተራማጅነትን የሚደግፍ የፈጠራና የጠያቂ ባህል ኮትኩተን እናሳድጋለን።

### ፍትህ

**እምነታችን** እያንዳንዱንአ ማንኛውም ተማሪ ትኩረት የሚገባው መሆኑ፤ ውጤቶች በዘር፣ በትውልድ፣ ወይም በማህበራዊ/ኤኮኖሚያዊ ደረጃ መተንበይ እንደሌለባቸው፤ ፍትህ በወገኖች መካከል የውጤት ክፍተት እንዳይኖር መጠየቁን፤ እና ለተማሪዎችና ለመምህራን የወደፊት እድሎች እንዲኖራቸው ሁኔታዎች መፍጠርና ማጠናከር ነው።

**ስለዚህ**፣ ሁሉንም ተማሪዎችና መምህራን ለከፍተኛ ደረጃ አንጠብቃቸዋለን፤ ሁሉም ተማሪዎች እንዲያተርፉ ተጨማሪ ድጋፎችና ጣልቃገብነቶች ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑትን መገልገያዎች እናሰራጫለን፤ ለተማሪዎች ስኬት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ የአስተዳደር መዋቅሮች አካላትን ለይተን እናስወግዳቸዋለን፤ በሁሉም መማርያ ክፍሎችና የስራ ቦታዎች በሞላ ፍትሃዊ የአሰራር ልምዶች ስራ ላይ መዋላቸውን እናረጋግጣለን።

አሳታሚው Department of Materials Management for the Office of the Superintendent of Schools
ትርጉም በLanguage Assistance Services Unit
Division of ESOL/Bilingual Programs • Office of Curriculum and Instructional Programs
1582.13 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 7/13 • Amharic